በዳዊት ምትኩ

# ዉዳሴ ዘኢሳያስ(ፕሬዝደንት)

ግርምት ማለት የማይሆን ወይም ይሆናል ተብሎ የማይታሰብ ነገር ሆኖ ማየት ወይም መስማት ይመስለኛል፡፡ እናም መሰንበቻዉን ከኢሳት ራድዮና ቴሌቪዥን ስለ አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ የሚተላለፈዉ ሁሉ ግርምት ፈጥሮብኛል፡፡

ሰዉዬዉ ለጋዜጠኞች ሰጡ በተባለ ቃለ ምልልስ ስለኢትዮጲያ አንድነት አሳቢና ተጨናቂ መሆናቸዉ ተገለጸ መባሉ፤ ይህ አልበቃ ብሎ ምስክር ነን ባዮች የነገሩን እዉነታነት እናረጋግጣለን ብለዉ መቅረባቸዉ ግርምቴን ጨምሮታል፡፡ መቼም የማስበዉ አጥቼ የረባ ያልረባዉን ሳነሳ ስጥል ዉዬ ባድር አቶ ኢሳያስ ስለኢትዮጲያ አንድነት አሳቢ ናቸዉ የሚል ለብልጭታ እንኳ ዉልብ የሚል ሃሳብ አይመጣልኝም፡፡ ኢሳቶች ግን ነገሩ ሀቅ ነዉ ብለዉ ደጋግመዉ እየገለጹልን ነዉ፡፡ ዘይገርም ነገር፡፡

‘ሁለት የኢሳት ጋዜጠኞች ወደ ኤርትራ ተጉዘዉ ፕሬዝደንት ኢሳያስን አነጋገሩ፤ …ፕሬዝደንቱም ኢትዮጲያ አሁን የምትገኝበት ሁኔታ እንደሚያስቆጫቸዉ ገለጹ፤ …ከሽግግሩ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጲያን የመሰለች ታላቅ ሀገር በዘር አትከፋፍሉ እያሉ ለወያኔ

ገዢዎች ምክር ቢለግሱም ሰሚ እንዳላገኙ ታወቀ’ እየተባለ የሚቀርበዉ ዘገባ አጃኢብ ነዉ፡፡

ነገሩ እንዴት ነዉ ጎበዝ፤ የአቶ ኢሳያስ ታሪክ ከመቶዎች ዓመታት በፊት የተፈፀመ አይደለም፡፡ በኛዉ ዘመን በቁማችን እያለን የሆነ ነዉ፡፡ ታዲያ ይህን የመሰለ በሬ ወለደ ታሪክ ከየት የመጣ ነዉ? እኔ’ኳ ነገሩ መሰማት በጀመረ ሰሞን ከቅርብ ወዳጆቼ ጋር ተወያይተንበት ትቼዉ ነበር፡፡ ኢሳቶች ግን ነገሩን ገፍተዉበት ቀጠሉ፤ ‘ኢሳት በዚህ ሳምንት’ በተሰኘ ፕሮግራም አንጋፋዉ ጋዜጠኛ አቶ ሙሉጌታ ሉሌ፤ የኮሚኒኬሽን ሚኒስትር ዴ’ኤታ የነበሩት አቶ ኤርምያስ ለገሠ፤ እንዲሁም ተወዳጁ ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና ቀርበዉ ይሆናል ብዬ ያላሰብኩት የአቶ ኢሳያስ አፍቃሪ አንድነት ሲመሰክርለት መስማቴ ይህቺን አጭር ጽሁፍ እንዳቀርብ ነቆረኝ፡፡

በፕሮግራሙ የቀረቡ እንግዶችም ሆኑ አወያዩ የተሰማቸዉን እንደተናገሩ እኔም በነፃ አስተሳሰብ የተሰማኝን ልግለጽ፤ አስቀድሜ ለሁሉም ያለኝን አክብሮትና አድናቆት ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡ እንደ‘ኔ ያለ ሥም የለሽ ጽሁፍ አቅራቢ የሚሰነዝረዉ ሃሳብና አገላለጽ ቅሬታ እንደማይፈጥርባቸዉ እምነቴ ነዉ፡፡ የተሰማኝን ያለ ፍርሃትና ሃፍረት ዉስጤን

እንዳመለከተዉ ከማቅረብ ዉጭ ሌላ ፍላጎት እንደሌለኝ ተረድተዉ በሰፊ ልቦና እንዲቀበሉኝም እጠይቃለሁ፡፡

ነገር የማይገባኝ ወይም ከጊዜ ጋር መራመድ የማይቻለኝ ሆኜ እንደሆን ባላዉቅም አቶ ኢሳያስንና የኢትዮጲያን አንድነት አዛምዶ ማሰብ ከቶም አይቻለኝም፤ ነገር በሶስት ይፀናል እንዲሉ ለዚህ እምነቴ መሠረት የሆኑኝን ሶስት ምክንያቶች ልግለጽ፡፡

አንደኛ- አቶ ኢሳያስ ከታሪክም ሆነ ነባራዊ እዉነታ ያፈነገጠ የቅኝ ግዛት ጥያቄ በማንሳት ኤርትራን ከኢትዮጲያ ለመገንጠል 30 ዓመት ሙሉ የተዋጉና ያዋጉ ሰዉ ናቸዉ፡፡ እኚህ ሰዉ ኢምንት ፍንጣቂ የአንድነት መንፈስ በዉስጣቸዉ ቢኖር ኖሮ ሃሳባቸዉን ለመቀየር ከበቂ በላይ ጊዜ ነበራቸዉ፡፡ ይህን ያህል ዘመን ኢትዮጲያዉያንን በጥይት አሩር ቆልተዉ ከፍተኛ የሕይወትና የሀብት ዉድመት አድርሰዉ ከተገነጠሉ በኋላ ስለ ኢትዮጲያ አንድነት አሳቢ ናቸዉ የሚለን ሰዉ አንድም የሚናገረዉን አያዉቅም፤ወይም የሚያዉቀዉን የማይናገር አድር ባይ ነዉ፤ ወይም ሕዝብ አያዉቅም የሚል ንቀት የተጠናወተዉ ነዉ፤ አልያም በቁም ላሞኛችሁ ባይ ነዉ፡፡

አቶ ኢሳያስ ኤርትራን ከገነጠሉ ወይም እንደ እርሳቸዉ አባባል 'ከቅኝ ግዛት' ነፃ ካወጡ በኋላ 'ኢትዮጲያ ሌላን ሀገር በቅኝ የያዘች ብቸኛ የጥቁር ሀገር ናት' በማለት ከአንድነት ጋር እስከወዲያኛዉ የማይታረቅ ቅራኔ እንዳላቸዉ ያረጋገጡ ሰዉ ናቸዉ፡፡ ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ ይህቺን የቅኝ ግዛት ጉዳይ ዕድሜ ልኩን ሲያላምጣት የነበረዉ ቀንደኛዉ የሕወሃት መስራችና ታጋይ ስብሃት ነጋ በስተመጨረሻ አቅለሸልሻዉ ተፍቷታል፡፡ 'የወጉሽ ሁሉ ይሰግዱልሻል' ማለት እንዲህ ይሆን?

ሁለተኛ- ሕወሃት የተባለን በዘር ላይ የተመሠረተ እና ከፋፋይነትና ዘረኝነት ዋነኛ መገለጫዉ የሆነን ድርጅት ከጨቅላነት ጀምሮ ያሳደገ፣ ያስታጠቀና በተለያዩ የጦር አዉዶች አብሮ በመሰለፍ እጁን ይዞ እየመራ አዲስ አበባ ያስገባ የአቶ ኢሳያስ ሻዕቢያ መሆኑ እንዴት ይዘነጋል? ይህን በጠራ ሰማይ እንደ ፀሐይ ፍንትዉ ብሎ የተቀመጠን እዉነታ ወደ ጎን በመተዉ አቶ ኢሳያስ በኢትዮጲያ ላይ የተንሰራፋዉን ዘረኛ ሥርዓት ተቃወሙ እየተባለ መነገሩ ወደር የሌለዉ የዘመናችን ስላቅ ነዉ፡፡ ሰዉዬዉ በዘር የመከፋፈልን ጉዳይ ተገቢ አለመሆን ከሽግግሩ ጊዜ ጀምሮ ገልጫለሁ ብለዉ ዛሬ ላይ ቢናገሩ አይገርመንም፣ ከቁም ነገርም አንቆጥረዉም፣ ሰምተን እንዳልሰማን እናልፈዋለን፣

'ኢትዮጲያ በቅኝ ገዝታናለች' ከማለት ያልተመለሱ ደፋር መሆናቸዉን አንዘንጋ ፤ ያ ሀገራችን ላይ የሞተዉ ሰዉዬ ሳይቀር ዛሬ  በሕይወት ቢኖር ኖሮ 'ኢሳያስን አትስሙት፤ እብድ ነዉ' ይለን ነበር፡፡ ታዲያሳ የኛ ብለን የምንኮራባችሁ ጋዜጠኞችና ወገኖች ምን ዞራችሁ? በግልጽ የተቀመጠዉን ሰወረባችሁ? የሰዉን ማንነት ከንግግሩ ብቻ ሳይሆን ከቀደመ ግብሩ ፈልፍላችሁ አዉጥታችሁ  የምትተነትኑና የምታሳዩ ስትሆኑ አሁን ምነዉ አንደበታችሁ ክፉኛ አዳጠዉ? ግርምት፡፡

ሶስተኛ- በአሁኑ ጊዜ ወያኔን በትጥቅ ትግል ለመጣል በኤርትራ ጦር አደራጅተዋል የሚባሉ ተቃዋሚ ኃይሎችን እንመልከት፤ ኢሳትን ጨምሮ በተለያዩ መገናኛዎች እንደሚገለጸዉ ከአርበኞች ግንባር እና ግንቦት ሰባት ሕዝባዊ ኃይል ዉጪ ሌሎቹ በዘር የተደራጁ ኃይሎች ናቸዉ፡፡ የኦሮሞ፤አማራ፤ትግሬ፤ቤንሻንጉል ወዘተ ነፃ አዉጪ የሚባሉ ድርጅቶች ይገኙባቸዋል፡፡ አቶ ኢሳያስ እዉነት የኢትዮጲያ አንድነት የሚያሳስባቸዉ ከሆነ ወደ ኢትዮጲያ አሻግረዉ ከመመልከት ይልቅ እዛዉ በጉያቸዉ አቅፈዉ የያዙዋቸዉን በዘር የተደራጁ ተቃዋሚዎች በአንድ ጠንካራ ብሔራዊ ድርጅት ጥላ ሥር አለማሰባሰባቸዉ ስለምን ነዉ? ቢያንስ ሙከራ ማድረጋቸዉ ሲገለጽ አለመስማታችን ምስጢሩ ምን ይሆን? ነገሩን አጥርቶ

የሚያይ ሰዉ አቶ ኢሳያስ የአንድነት አርበኛ መሰኘታቸዉ ባዶ የወናፍ ንፋስ መሆኑን ከዚህ መረዳት አይሳነዉም።

ሁለቱ የኢሳት ጋዜጠኞች ወደ ኤርትራ መጓዛቸዉ ከተነገረ ጀምሮ ስለ አቶ ኢሳያስ የሚነገረዉ ሁሉ ከዘገባ ይልቅ ፕሮፖጋንዳ ይመስላል። የሰዉዬዉን ሰብዕና አጉልቶ ለማቅረብ ከላይ ታች ይባላል። ጋዜጠኞቹ ከኤርትራ መልስ ዓለም ለምኔ ብለዉ በተለያዩ ሀገራትና የሰሜን አሜሪካ ግዛቶች እየተዘዋወሩ የጋዜጠኛ አይሉት ካድሬ ሥራ ተጠምደዋል። የኢትዮጲያ መጪ ተስፋ በሰዉዬዉ እጅ ብቻ ያለ ይመስል ኢትዮጲያዉያን ድጋፍ እንዲሰጡ እየቀሰቀሱ ነዉ። እኛ ኢትዮጲያዉያን አርባ ቦታ መከፋፈላችንን ትተንና፤ እንደቀደሙ አባቶቻችን በአንድ ልብ መክረን ሀገራችንን መታደግ አቅቶን ከዚህ ሁሉ ችግር የከተተን ሰዉ ጉያ ዉስጥ ገብተን ስናንቆለጳጵሰዉ መገኘታችን እንደ ዜጋ በቁም መሞታችንንና ክብራችንን መሸጣችንን ያረጋግጣል። ይህ አባባል እንደሚከብድ ብረዳም ከእዉነታዉ እንደማይርቅ ይሰማኛል። የእሳት ልጅ አመድ የተባለዉ በኛ ተፈጽሟል ወገኔ።

ነገሬ ሳይንዛዛ አንዲት ግርምት ልጨምርና ልሰናበት።

አቶ ኤርሚያስ ለገሠ ከላይ በጠቀስነዉ የኢሳት ዝግጅት ላይ አቶ ኢሳያስ አማርኛ አለመናገራቸዉ የጥላቻ ሳይሆን መናገር

ስለረሱ መሆኑን፤ ይህንንም ከአቶ ያሬድ ጥበቡ የተረዱ መሆኑን መግለፃቸዉ ግራሞት ብቻ ሳይሆን የኮረኮሩኝ ያህል አስቆኛል፡፡ ቀድሞ ነገር እንደ አቶ ኤርምያስ ያለ የወያኔ ባለሥልጣናትንና በአራድኛዉ አባባል ከእነርሱ ጋር ሙድ የገጠሙን ሰዎች ሰብዕና አብጠርጥሮ የሚያዉቅ ሰዉ አቶ ያሬድን በአስረጅነት መጥቀሱ ያስደምማል፡፡

ይህ ቢቀር አቶ ኢሳያስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸዉን በደሴ ከተማ ያጠናቀቁ መሆኑ እየታወቀ፤ ከዚያ ዕድሜ በኋላ ቋንቋዉን ረሱ መባሉ ማንን ያሳምናል፤ አንድ የሚናገረዉን ያዉቃል ተብሎ የሚታመን ሰዉ በመላዉ ዓለም የሚሰራጭ ሚዲያ ላይ ቀርቦ የሚሰጠዉን መረጃ ተዓማኒነት እንዴት አስቀድሞ አይመዝንም፤ ደግሞ'ኮ ሰዉዬዉ በረሃ የገቡት በጊዜዉ የኢትዮጲያ አካል ወደ ነበረችዉ ኤርትራ እንጂ ባህር ተሻግረዉ አልሔዱም፤ ያን ሁሉ ዘመን ጦር ሲመሩ በወቅቱ ከነበረዉ መንግሥት በአማርኛ ይተላለፍ የነበረዉን የመገናኛ ስርጭት አይሰሙም ወይም አይረዱም ነበር ብሎ መገመት አዳጋች ነዉ፡፡ይህች የአቶ ኤርምያስ አባባል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸዉን በጨረሱበት ዕድሜ ወይም ከዚያ ቀደም ባለ ዕድሜያቸዉ ባህር ማዶ ተሻግረዉ ለበርካታ ዓመታት በዉጭ ሀገር የኖሩንና አማርኛ አጣርተዉ የሚናገሩ ወገኖቻችንን ይበልጥ ሳታስገርም አትቀርም፡፡

ወገኔ፣ ይህ ሁሉ ዲስኩርና ቆረጣ ቅጠላ እየቀረበ ያለበትን ምክንያት በአንክሮ ልንመረምር ይገባል፣ የአቶ ኢሳያስ አለባበስ ሳይቀር እየተጋጋለ የሚቀርብልን ለአንድነት አላቸዉ የሚባለዉ ጽኑ እምነት አልዋጥ ብሎ እየተናነቀን የግድ እንድንጋት የሚደረግበትን ምክንያት መጠየቅ አለብን ፤ ይህን አድራጊዎቹ ደግሞ ብዙ ያዉቃሉ ብለን የምናከብራቸዉ ወገኖቻችን መሆናቸዉ ነገሩን በጥብቅ እንድናስብበት ግድ ይለናል፡፡

‘ ከአቶ ኢሳያስ አመራር ጋር ወደፊት!’ ዓይነት መፈክር የምታሰሙን ወገኖቻችን ሁሉ፤ አብዛኛዉ ኢትዮጲያዊ በአቶ ኢሳያስ ላይ ከፍተኛ ጥርጣሬ እንዳለዉ አትዘንጉ፡፡ አሁን እንደምታደርጉት የማይመስል ነገር ይዛችሁ ቀርባችሁ ቀርቶ ሰዉዬዉ ብረት ያነሱ ተቃዋሚዎችን እየረዱ ነዉ የሚባለዉን እንኳ ከበስተኋላዉ ምን መዘዝ ይኖረዉ ይሆን በማለት በአንክሮ እየተከታተለዉ ነዉ፡፡

በኢትዮጲያና ኤርትራ ሕዝቦች መካከል መቀራረብ መፍጠሩ ጠቀሜታዉ ባይካድም በከፍተኛ ብልሃትና ጥንቃቄ መያዝ ያለበት ጉዳይ ነዉ፤ ትብብር የመፍጠሩም ሂደት በሕዝብ በተመረጡ መንግሥታት ደረጃ በሚደረግ

መፈቃቀድና ግንኙነት የሚመራ እንጂ አሁን እናንተ 'የኤርትራን ሕዝብ በየሻይ ቤቱና ታክሲ ላይ በማነጋገር ስሜቱን ተረድተናል' እያላችሁ እንደምታራግቡት አይሆንም፡፡

ኢትዮጲያና ኤርትራ ከአንድ ወደ ሁለት ሀገራት የተከፈሉት ቁጠማ ጎዝጉዘዉ በሠላም ተመራርቀዉ አይደለም፤ በሁለቱም ወገን በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ሕይወት ተሰዉቷል፤ ከፍተኛ ንብረት ወድሟል፤ እስካሁን የሚያወዛግብ የፖለቲካ ቁማር ተሰርቷል፡፡ ዘላቂና መተማመን ያለበት ግንኙነት እንዲፈጠር ይህ ሁሉ ነጥሮ ወጥቶ ድርድር መደረግ አለበት፡፡ እናም የኢሳት ጋዜጠኞችም ሆናችሁ ሌሎች ወገኖቻችን የምታነበንቡትን ዉዳሴ ዘኢሳያስ አቁሙና ማስተዋልን ገንዘብ አድርጉ፡፡መቼም ወገኖቼ ናችሁና ጨዉ ሆይ ለራስህ ስትል ጣፍጥ ብዬ አልተርትባችሁም፤ 'ያዋከቡት ነገር እኔን አላማረኝም' የሚለዉን የጥልዬን ተወዳጅ ዘፈን ሳልጋብዛችሁ ግን አላልፍም፡፡

እንግዲህ አወነጋግሬም ቢሆን ሃሳቤን ያስተላለፍኩ ይመስለኛል፤ በሥም የጠቀስኳችሁ ወገኖቼ ሃሳቤን እንደ ወዳጅ ወቀሳ እንጂ አንደጠላት በትር አትዉሰዱብኝ፤ እናንተ የሠራችሁትንና የምትሠሩትን ያህል ሥራ የለኝምና አክባሪያችሁ ነኝ፡፡ ስለ አቶ ኢሳያስ የምታቀርቡት ዝግጅት

ክፉኛ የቆጠቆጠኝ ከአክብሮቴ የተነሳ መሆኑን ተረዱልኝ፡፡

ቸር ያሰንብተን፡፡

- maknolfirst@gmail.com